5ኛ ዓመት ቁጥር 45 5th year №. 45	ባህር ዳር የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም. Bahir Dar 9th March 2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKR HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 0.90	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 p.O.BOX

ማውጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 45/1992 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለተፈቀደ የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና አዋጅ ገጽ 2	Proclamation№ 45/2000 A Proclamation that provides to Authorize Domestic Borrwing and issue Security in the Amhara national Regional State. Page 2

አዋጅ ቁጥር 45/1992 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለተፈቀደ የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና አዋጅ

የክልሉን የግብርና ልማት ለማፋጠን የአብዛኛውን አርሶ አደር ምርትና ምርታማነት ማሳደግ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

እራሳቸውን ችለው መበደር ለማይችሉ ድሃ አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎት ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49/3/9/1 እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 33 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

PROCLAMATION№ 45/2000
A PROCLAMATION THAT Provides TO AUTHORIZE DOMESTIC Borrowing AND ISSUE SECURITY IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

WHERE AS, it has become necessary to increase most farmers' agricultural production so as to accelerate agricultural development of the region.

WHERE AS, it has become vital to provide credit service for those poor farmers that they can't get credit by their own,

NOW, THEREFORE, pursuant to sub article 3/9/1 article 49 of the regional constitution and article 33 of the finance administration proclamation of the region, The Council Of Amhara National Regional State is here by proclaimed as follows.

1. Short Title

ይህ አዋጅ " በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለተፈቀደ የአገር ውስጥ ብድርና ዋስትና የወጣ አዋጅ ቁጥር 45/1992 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ስለመበደር</u>

የክልሉን የግብርና ምርታማነት ለማሣደግ ለ1992/93 የምርት ዘመን ለግብዓት ግዥና ለእንስሳት ፓኬጅ ማስፈፀሚያ ይውል ዘንድ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋስትና ከብር 170,000,000 /አንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን/ ያልበለጠ ከአገር ውስጥ ባንኮች ለመበደርና ከአርሶ አደሩ ጋር ቁርኝትና ብድር የማስተዳደር ብቃት ካላቸው ተቋማት ጋር ስምምነት በማድረግ ለአርሶ አደሩ ብድር መስጠት እንዲችሉ ዋስትና ለመስጠት ተፈቅዷል።

3. <u>የጊዜ ገደብ</u>

የተፈቀደው የብድርና የወሰትና መጠን እስከ ሰኔ 30/1993 ዓ.ም የሚመለስ ይሆናል።

4. <u>የአስፈፃሚ አካል ስልጣን</u>

ብድሩንና ዋስትናውን እየተከታተለ እንዲያስፈጽም በዚህ አዋጅ ለገንዘብ ቢሮ ስልጣን ተሰጥቶታል።

5. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከዛሬ የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ምክር ቤት

This Proclamation may be cited as "The proclamation to Authorize Domestic Borrowing and Issue Security in the Amhara National Regional State No. 45/2000."

2. Borrowing

It is authorized to borrow money which is not exceeding birr 170 million from domestic banks on be half of the Amhara National Regional State for the provision of modern agricultural inputs for 2000/2001 production year and to issue security by making agreement with institutions that are related to farmers and efficient to manage credit, to develop the regional agricultural production.

3. Time Limit

The authorized loan and security amount shall be paid back until July 7/2001.

4. Power of the Executing body

The bureau of finance, pursuant to this proclamation, is here by empowered to under take all acts necessary for the utilization of the loan and security issued.

5. Effective Date

This proclamation shall be entered in to force from the date

Done at Bahir Dar

This 9th day of March 2000

The Council Of The Amhara National Regional State.